በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የባህር ዳር ዩኒቨርሲቲ
የ2009 በጀት ዓመት ሂሳብ ኦዲት ሪፖርት

ዩኒቨርሲቲው የተመደበለትን የመደበኛ በጀት ለታቀደለት ዓላማ ማዋሉን፣ እንዲሁም ሂሳቡ በመንግስት የሂሳብ አያያዝ ስርዓት መሰረት መያዙንና የመንግስት ሀብትና ንብረት በሚገባ መጠበቁን ለማረጋገጥ የ2009 በጀት ዓመት ሂሳብ ሪፖርቶችን እና የሂሳብ ማስታወሻዎችን ኦዲት አድርገናል፡፡

የሂሳብ ሪፖርቶችን የማዘጋጀት ኃላፊነት የዩኒቨርሲቲው ስራ አመራር ሲሆን የሂሳብ ሪፖርቶችን ኦዲት በማድረግ ሙያዊ አስተያየት መስጠት ደግሞ የፌደራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት ኃላፊነት ነው፡፡

ኦዲቱ የተከናወነው የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤትን ለማቋቋም በወጣው አዋጅ ቁጥር 982/2008 ለመ/ቤታችን በተሰጠው ስልጣን ሲሆን፣ ዓለም አቀፍ የኦዲት ደረጃዎችን (ISSAI) መሠረት በማድረግ ነው፡፡ እነዚህን የኦዲት ደረጃዎች መከተል ኦዲቱን በሚገባ አቅደን በመሥራት በተዘጋጁት የሂሳብ መግለጫዎች ላይ አጥጋቢ የሆነ የኦዲት አስተያየት ለመስጠት ያስችለናል፡፡

ኦዲታችን፡-

- የሂሳብ መግለጫዎች ላይ የሰፈሩትን አሀዞችና መግለጫዎችን የሚደግፉ ማስረጃዎችን በናሙና ኦዲት ማከናወንን፣
- የሥራ አመራሩ የሂሳብ መግለጫዎችን ሲያዘጋጅ ያደረገውን ጉልህ ግምቶች እና ውሳኔዎችን መመዘንን፣
- የሂሳብ አያያዝ ፖሊሲዎች ከዓመት ዓመት ሳይቀያየሩ በሥራ ላይ መዋላቸውን እና በበቂ ሁኔታ መገለጻቸውን ማመዛዘንን፣ያጠቃልላል፡፡

ከዚህም በተጨማሪ የተዘጋጁት የሂሳብ መግለጫዎች ተገቢ የሆኑ አዋጆች፣ ደንቦች እና በተከታታጁ የወጡ መመሪያዎችን በመከተል የተዘጋጁ መሆኑን በናሙና ኦዲት ማከናወንን ይይዛል፡፡

የሂሳብ መግለጫዎች ጉልህ ከሆኑ ስህተቶች የፀዱ ለመሆኑ በቂ ማስረጃና አጥጋቢ ማረጋገጫ የሚሰጥ መረጃና ማብራሪያ ሊያስገኝ በሚችል መልኩ ኦዲቱን አቅደን አከናውነናል፡፡

ለኦዲቱ ሥራ መሠረት የሆኑት ዩኒቨርሲቲው ያቀረባቸው የሂሳብ መግለጫዎች፤ መዛግብት፤ ደጋፊ ማስረጃዎች እንዲሁም በዩኒቨርሲቲው ሥራ አመራር የተሰጡ ማብራሪያዎች ናቸው::

ኦዲቱ የተከናወነው የበጀት ዓመቱን የሂሳብ እንቅስቃሴ ሊወክሉ የሚችሉ ናሙናዎችን በመውሰድ በጥልቀትና በዝርዝር ኦዲት በማድረግ ነው::

የሚከተሉት የኦዲት ተደራጊው መ/ቤት የሂሳብ መግለጫዎች ከዚህ የኦዲት ሪፖርት ጋር ተያይዘው ቀርበ□ል::

- □□ቢ/የዕርዳታ/ የብድር ሂሳብ ሪፖርት፣
- የወጪ ሂሳብ ሪፖርት፣
- የዝውውር ሂሳቦች ሪፖርት፣
- የተሰብሳቢ ሂሳቦች ሪፖርት፣
- የተከፋይ ሂሳቦች ሪፖርት፣
- የሂሳብ ሚዛን ሙከራ፣

ለኦዲት አስተያየቱ መሰረት የሆኑት ጉዳዮች፣

የዩኒቨርሲቲው የሂሳብ መግለጫዎች ጉልህ የሆነ ግድፈት የሌለባቸው፣ በአዋጅ በተፈቀደው በጀት እና በመንግሥት ሂሳብ አያያዝ ሥርዓት መሠረት የተዘጋጁ እና የተሰበሰበው ገቢ፣ የተከፈለው ወጪና የበጀት አጠቃቀሙ የፋይናንስ አስተዳደር አዋጅን፤ ደንብና መመሪያን የጠበቀ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፡-

1. በመንግስት ሠራተኞች አዋጅ ቁጥር515/1999 አንቀጽ 6 ከንዑስ አንቀጽ 1-4 በዝርዝር እንደተደነገገው እንዲሁም በፌዴራል ሲቪል ሰርቪስ ኤጀንሲ በቁጥር ሲሰሚ30/ጠ10/71/390 በቀን10/18/8/03 በተጻፈው ደብዳቤ ማንኛውንም የመንግስት መስሪያ ቤት ሠራተኞች የደመወዝ ስኬል እና ጥቅማጥቅም ቀርቦ የሚወሰነው በሚኒስትሮች ምክር ቤት መሆኑ፤ በቦርድ ወይም በማኔጅመንት ከመደበኛ በጀት የሚወሰንና የሚከፈል ክፍያ ተቀባይነት እንደሌለው በግልፅ ተቀምጧል። ይሁን እንጂ የዩኒቨርሲቲው ሂሣብ ኦዲት ሲደረግ፤
   - በቴክኖሎጂ ኢንስቲትዩት የሬጅስትራር ሠራተኞች ከ1959 ጀምሮ የተመረቁ ተማሪዎች ወደ ሲስተም ያስገቡበት የሁለተኛ ዙር ክፍያ በሚል ብር 103,342.96 የተከፈለ መሆኑ፤

- ➢ በግሽ አባይ ግቢ የቴክኖሎጂ ኢንስቲትዩት በአስተዳደር ካውንስል ውሳኔ ከቴክኖሎጂ ኢንስቲትዩት ICT ሰራተኞች ጋር በቀጥታ ውል በመግባት የኢንተርኔት ዝርጋታ የሠሩበት በማለት ብር 113,300.00 የተከፈለ መሆኑ፤
- ➢ ለጠቅላላ ህክምና ባለሙያዎች እና እስፔሻሊስት ሀኪሞች የቶፕአፕና ክሊኒካል አሎዋንስ በየወሩ እንዲከፈላቸው በዩኒቨርሰቲው አስተዳደር ቦርድ በተወሰነው መሰረት ለህክምና ባለሙያዎች ለመደበኛ አገልግሎት ከደንብና መመሪያ ውጭ ብር 3,632,680.00 ከውስጥ ገቢ የተከፈለ መሆኑ፤

2. ለተለያዩ ዕቃዎችና አገልግሎቶች ግዢ ለተለያዩ አቅራቢዎች (ድርጅቶች) ተከፍሎ በወጪ ለተመዘገበው ብር 20,426,334.68 የቀረበው ማስረጃ የዱቤ ሽያጭ ደረሰኝ መሆኑ፤
3. በማዕከል ግቢ ለፍራሽና ትራስ ግዢ ለአማጋ ስፖንጅ ውጤቶች ማምረቻ ድርጅት ብር 6,369,000.00 እና በኢትዮጵያ ቴክስታይልና ፋሽን ቴክኖሎጂ ኢንስቲትዩት በሰላም ግቢ ውስጥ የኔትወርክ ማስፋፊያ ለተሰራበት ለላብራዶር አጠቃላይ ንግድ ኃ/የተ/የግ/ማህበር ብር 185,074.28፤ በድምሩ በብር 6,554,074.28 የዕቃና የአገልግሎት ግዢ ያለውድድር በቀጥታ የተፈጸመ መሆኑ፤
4. በጊዜ ገደቡ ያልተወራረደ ብር 8,280,384.39 ተሰብሳቢ ሂሳብ የሚገኝ መሆኑ፤
5. በ6416 ሂሳብ መደብ በበጀት ዓመቱ የተፈቀደ በጀት ሳይኖር ብር 120,000.00 ተከፍሎ መገኘቱ፤ በኦዲቱ ወቅት ታውቋል፡፡

ከላይ በተገለጹት ጉልህና መሠረታዊ ልዩነቶች የተነሣ በእኛ አስተያየት የዩኒቨርሲቲው የሂሳብ መግለጫዎች ሰኔ 30 ቀን 2009 ዓ.ም የተመለከተውን የፋይናንስ አቋም እና የበጀት ዓመቱን የሥራ እንቅስቃሴ በኢትዮጵያ መንግሥት የፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ እንዲሁም የሂሳብ አያያዝ ሥርዓት መሠረት በአጥጋቢ ሁኔታ አያሳዩም፡፡

<u>**ትኩረት ሊሰጥባቸው የሚገባቸው ጉዳዮች (Emphasis of Matters)**</u>

- ➢ ለዩኒቨርሲቲው በ2009 በጀት ዓመት የተፈቀደለት በጀት እና በሥራ ላይ የዋለው ሂሣብ ሲነጻጸር በተለያዩ ሂሳብ መደቦች ብር 48,864,676.92 ሥራ ላይ ያልዋለ (ያልተሰራበት) መሆኑ፤

<u>**ሌሎች ጉዳዮች፤**</u>

- ➢ የዩኒቨርሲቲው የንብረት አጠባበቅና አመዘጋገብ ኦዲት ሲደረግ በህክምናና ጤና ሳይንስ ኮሌጅ፤
- ➢ ዋጋቸው ሳይገለፅ ከውጭ ሀገር በእርዳታ የመጡ ዕቃዎች በኮሚቴ ዋጋቸው ተተምኖ መመዝገብ ሲገባቸው ዋጋ ሳይወጣላቸው የተመዘገቡ መሆኑ፤

- ዋጋቸው በዶላር ተገልጾ ከውጭ ሀገር በእርዳታ የመጡ ዕቃዎች በሀገሪቱ መገበያያ ገንዘብ (ብር) ሳይቀየር የተመዘገቡ መሆኑ፤
- በአላቂ እና በቋሚ ዕቃዎች ግምጃ ቤት አካባቢ የማገዶ እንጨት ክምችት የሚገኝና ለምግብ ቤት ቅርበት ያለው በመሆኑ አደጋ እንዳያደርስ ተገቢ የማስተካከያ እርምጃ መውሰድ የሚስፈልግ መሆኑ፤

በኦዲቱ ወቅት ታውቋል፡፡

ፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

ባህር ዳር ዩኒቨርሲቲ

የ2009 በጀት ዓመት ሂሳብ ኦዲት ግኝቶችና የማሻሻያ ሃሳቦች

መግቢያ

የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤትን ለማቋቋም በወጣው አዋጅ ቁጥር 982/2008 ለመ/ቤታችን በተሰጠው ሥልጣን መሰረት የባህር ዳር ዩኒቨርሲቲ የ2009 በጀት ዓመት ሂሳብ ላይ የኦዲት አስተያየታችንን ለመስጠት ያስችለን ዘንድ የዩኒቨርሲቲውን ሂሳብ ኦዲት አድርገናል፡፡

ዓላማ

የዚህ ሪፖርት ዓላማ በኦዲታችን ወቅት የተገኙትን የውስጥ ቁጥጥር ድክመቶች እና ሌሎች ግድፈቶች የዩኒቨርስቲው የበላይ አመራር አካላት እንዲያውቁትና ተገቢውን የማስተካከያ እርምጃ በመውሰድ ምላሽ እንዲሰጡበት ለማስቻል ነው፡፡

የኦዲቱ ወሰንና ኃላፊነት

ኦዲቱ የተከናወነው ዓለም አቀፍ የኦዲት ደረጃዎችን (ISSAI) መሰረት በማድረግ ነው፡፡ እነዚህን የኦዲት ደረጃዎች በመከተል ኦዲቱን በሚገባ አቅደን በመስራት በተዘጋጁት የሂሳብ መግለጫዎች ላይ የኦዲት አስተያየት ለመስጠት ያስችለናል፡፡

ኦዲታችን፣

- የሂሳብ መግለጫዎች ላይ የሰፈሩት አሀዞችና መግለጫዎችን የሚደግፉ ማስረጃዎችን በናሙና ኦዲት ማከናወንን፣
- የሥራ አመራሩ ሂሳብ መግለጫዎችን ሲያዘጋጅ ያደረጋቸው ጉልህ ግምቶች እና ውሳኔዎች መመዘንን፣
- የሂሳብ አያያዝ ፖሊሲዎች ከዓመት ዓመት ሳይቀያየሩ በሥራ ላይ መዋላቸውን እና በበቂ ሁኔታ መገለጻቸውን ማመዛዘንን ያጠቃልላል፡፡

ከዚህም በተጨማሪ ኦዲቱ የተዘጋጁት የሂሳብ መግለጫዎች ተገቢ የሆኑ አዋጆች፣ ደንቦችና መመሪያዎችን በመከተል የተዘጋጁ መሆናቸውን ኦዲት ማድረግን ይጨምራል፡፡

አስተያየት ላይ ለመድረስ በሂሳብ መግለጫዎች ላይ ያለውን የመረጃ አቀራረብ አጠቃላይ ብቃት ገምግመናል፡፡

ይሁን እንጂ ኦዲቱ በባህር ዳር ዩኒቨርሲቲ የሚታዩትን የውስጥ ቁጥጥርና ሌሎች ድክመቶችን ሙሉ በሙሉ ሊያሳይ አይችልም፡፡

የሂሳብ መግለጫዎችን የማዘጋጀት ኃላፊነት የዩኒቨርሲቲው ሥራ አመራር ሲሆን፣ የሂሳብ መግለጫዎችን ኦዲት በማድረግ ሙያዊ የኦዲት አስተያየት መስጠት ደግሞ የፌደራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት ኃላፊነት ነው፡፡

የባህር ዳር ዩኒቨርስቲ የ2009 በጀት ዓመት ሂሳብ ኦዲት ግኝቶችና የማሻሻያ ሀሳቦች ከዚህ እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

1. <u>**የወጪ ሂሳብ፣**</u>

በወጪ የተመዘገቡት ሂሳቦች ተቋሙ ለተጠቀመበት አገልግሎት መዋሉን፤ የዕቃና አገልግሎት ግዥ በመንግስት የግዥ መመሪያ መሠረት መፈፀሙን፣ የተገዙት ዕቃዎች ገቢ መደረጋቸውንና እንዲሁም ለታቀደለት ዓላማ መዋላቸውን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣ ቀጥሎ የተመለከቱት ሁኔታዎች ተገኝተዋል፡፡

1.1 <u>**ደመወዝና ጥቅማጥቅም፤**</u>

1.1.1.1 <u>**ግኝት፤ ለህክምና ባለሙያዎች፤ ለመምህራንና ሌሎች ሠራተኞች ስለተፈጸመው ክፍያ፤**</u>

የፌዴራል መንግስት የፋይናንስ ኃላፊነት መመሪያ ቁጥር 6/2003 ክፍል ሁለት የፋይናንስ ኃላፊነት የመንግስት መ/ቤቶች የበላይ ኃላፊዎች ቁጥር 6(ለ) የፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ እንዲሁም አዋጁን ለማስፈፀም በወጣው የፋይናንስ አስተዳደር ደንብ ላይ በመመርኮዝ የወጡት መመሪያዎች በመ/ቤት ውስጥ በተሟላና ተገቢ በሆነ መንገድ ሥራ ላይ መዋላቸውን በማረጋገጥ ረገድ ላይ ተጠያቂነት እንዳለባቸው ይገልፃል፡፡ በፌዴራል ሲቪል ሰርቪስ ኤጀንሲ በቁጥር ሲሰሚ30/ጠ10/71/390 በቀን10/18/8/03 በተጻፈው ደብዳቤ ማንኛውንም የመንግስት መስሪያ ቤት ሠራተኞች የደመወዝስኬል እና ጥቅማጥቅም ቀርቦ የሚወሰነው በሚኒስትሮች ምክር ቤት መሆኑ፤ በመንግስት ሠራተኞች አዋጅ ቁጥር515/1999 አንቀጽ 6 ከንዑስ አንቀጽ 1-4 በዝርዝር እንደተደነገገው በቦርድ ወይም በማኔጅመንት የሚወሰንና የሚከፈል ክፍያ ተቀባይነት እንደሌለው በግልፅ ተቀምጧል፡፡ ይሁን እንጂ የዩኒቨርሲቲው ሂሣብ ኦዲት ሲደረግ፤

- **በማዕከል ግቢ** ለጠቅላላ ህክምና ባለሙያዎች እና እስፔሻሊስት ሀኪሞች የቶፐአፕና ክሊኒካል አሎዋንስ በየወሩ እንዲከፈላቸው በዩኒቨርሰቲው አስተዳደር ቦርድ በተወሰነው

መሰረት ለህክምና ባለሙያዎች ከደንብና መመሪያ ውጭ ብር 3,632,680.00 ከውስጥ ገቢ ተከፍሎ ተገኝቷል፡፡ ዝርዝሩ በሰንጠረዡ ተመልክቷል፡፡

ተ.ቁ	ቀን	የደረሰኝ አይነት	የደረሰኝ ቁጥር	የሂሳብ መደብ	የባለሙያዎች (ዶክተሮች) ብዛት	የገንዘብ መጠን
1	07/03/09	BPV	69927	6116	249	383,100.00
2	05/04/09	BPV	55432	6116	255	396,000.00
3	25/04/09	BPV	43137	6121	272	418,500.00
4	10/06/09	BPV	0845419	6116	270	425,700.00
5	05/07/09	BPV	0845506	6116	272	430,500.00
6	29/07/07	BPV	006430	6116	81	625,840.00
7	27/10/09	BPV	43274	6116		577,440.00
8	15/02/09	BPV	69863	6121		375,600.00
					ድምር	3,632,680.00

- **በቴክኖሎጂ ኢንስቲትዩት** የሬጅስትራር ሠራተኞች ከ1959 ጀምሮ የተመረቁ ተማሪዎች ወደ ሲስተም ያስገቡበት የሁለተኛ ዙር ክፍያ በሚል በቀን 21/04/09 በባንክ ወጪ ማስመስከሪያ ቁጥር 241565 በሂሳብ መደብ 6116 ብር 103,342.96 ተከፍሎ ተገኝቷል፡፡
- በግሽ አባይ ግቢ የቴክኖሎጂ ኢንስቲትዩት በአስተዳደር ካውንስል ውሳኔ መሠረት ያለውድድር ከICT ሰራተኞች ጋር በቀጥታ ውል በመግባት የኢንተርኔት ዝርጋታ አገልግሎት የሠሩበት በማለት በቀን 11/07/09 በባንክ ወጪ ማስመስከሪያ ቁጥር 038634 በሂሳብ መደብ 6251 ብር 113,300.00 ተከፍሎ ተገኝቷል፡፡

1.1.1.2 ስጋት፤

ክፍያዎች በመንግስት ደንብና መመሪያ መሰረት ተግባራዊ ካልተፈጸሙ የመንግሰት ሀብት ለብክነት ሊጋለጥ ይችላል፡፡

1.1.1.3 **የማሻሻያ ሀሳብ፤**

ክፍያዎች በመንግስት ደንብና መመሪያ መሠረት እንዲፈጸሙ የዩኒቨርሲቲው ሥራ አመራር ተገቢ የማስተካከያ እርምጃ መውሰድ ይኖርበታል፡፡

1.1.1.4 **የሚመለከተው ኃላፊ ምላሽ፤**

- በዩኒቨርሲቲው ህክምናና ጤና ሳይንስ ኮሌጅ ለሚያስተምሩ ስፔሻሊስት ሐኪሞችና ለሐኪሞች ቶፕአፕ እና ክሊኒካል አልዋንስ የተከፈለው ዩኒቨርሲቲው በሀገሪቱ ካለው የሀኪም እጥረት አኳያ የተከፈተውን ፕሮግራም ለማስቀጠልና ትምህርት የጀመሩ ተማሪዎች ትምህርታቸውን እንዳያቋርጡ

የግድ ስለሆነ የችግሩን አሳሳቢነት ለዩኒቨርስቲው ስራ አመራር ቦርድ ቀርቦ ቦርዱ በከፍተኛ ትምህርት አዋጅ 650/2001 አንቀጽ 44/1 በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የውስጥ ገቢ አስተዳድር መመሪያ ቁጥር 39/2006 አንቀፅ 5/2/ (ሀ) በተሰጠው ኃላፊነት መሰረት የችግሩን አሳሳቢነት በመረዳት በቦርድ ውሳኔ ቁጥር 005/2008 በቀን 03/08/2008 ከውስጥ ገቢ እንዲከፈላቸው የተወሰነ ሲሆን ለገ/ኢ/ት/ሚ/ር እና ለፐብሊክ ሰርቪስና የሰው ሀብት ልማት ሚኒስቴር በቁጥር 21/1994/2.7.1/ በ07/09/09 የክፍያ ተመን እንዲአፀድቁልን ወይም ተመጣጣኝ ጥቅማጥቅም እንዲወስኑልን በደብዳቤ አሳውቀን መልስ እየተጠባበቅን ሲሆን መልስ አስኪሰጠን ድረስ ዩኒቨርሲቲው ተልኮዉን ለመፈፀም ካለበት የሀኪሞች እጥረት አኳያ ቦርዱ በወሰነው ውሳኔ እየከፈልን ቢሆንም ከ2010 በጀት ዓመት ጀምሮ ለስፔሻሊስት ሐኪሞች ካልሆነ በስተቀር ለማናቸውም ሐኪም ክፍያ የቆመ መሆኑን እየገለፅን ለገ/ኢ/ት/ሚ/ር እና ለፐብሊክ ሰርቪስና የሰው ሀብት ልማት ሚኒስቴር የፃፍነው ደብዳቤና የቦርድ ውሳኔ ያያዝን ስለሆነ ግኝቱ እንዲሰረዝ እንጠይቃለን፡፡

- በቴክኖሎጅ ኢንሲቲትዩት ከ1959 ዓ.ም ጀምሮ የተመረቁ ተማሪዎች የትምህርት ዳታ ወደ ሲስተም ለማስገባት በትርፍ ሰዓት ለማሰራት ከሲቪል ሰርቪስ ሚ/ር ያስፈቀድን ቢሆንም በትርፍ ሰዓት ማሰራቱ ስራውን በፍጥነት ከማጠናቀቅ አንፃር እና ለቁጥጥር አመች ባለመሆኑ ከሌሎች ዩኒቨርሲቲዎች ተሞክሮ ተወስዶ በኢንሲቲትዩቱ ማኔጅመንት ተወስኖ ስራው እየተሰራና ክፍያውም በውሳኔው መሰረት የአንድ ተማሪ ፋይል በአስገቡት መጠን የከፈልን ሲሆን መረጃዎችን በኮምፒውተር ሲስተም በቀላሉ ባለጉዳይን ለማስተናገድ እና መረጃዎችን ከመጥፋት ለመታደግ ታስቦ የተሰራ መሆኑን ግንዛቤ እንዲያዝልን፡፡
- በግሽ አባይ ግቢ የሚማሩ የቴክኖሎጅ ተማሪዎች በላብራቶሪያቸው የኢንተርኔት አክሰስ የሌላቸው በመሆኑ ያነሷቸውን ጥያቄዎች ለመፍታት በግዥ ሂደት ለማከናወን ቢታሰብም ተማሪዎቹ የሚገቡበት ጊዜ የተቃረበ በመሆኑ በቴክኖሎጅ ኢንሲቲትዩት የሚገኙ መምህራን የሚሰሩበትን ፕሮፖዛል እንዲያቀርቡ ተጠይቆና ድርድር ተደርጎ ለኢንሲቲትዩቱ ማኔጅመንት ቀርቦ ሰፊ ውይይት ተካሂዶበት የተማሪዎቹን ችግር በፍጥነት ከመፍታት አንፃር የተሰራ መሆኑን ግንዛቤ ቢያዝልን፡፡

1.1.1.5 <u>የኦዲተሩ አስተያየት፤</u>

- የመንግሥት ሠራተኞች ጥቅማጥቅም የሚወሰነው በሚኒስትሮች ምክር ቤት በመሆኑ ለጤና ባለሙያዎች የሚከፈለው የቶፐአፐና ክሊኒካል አሎዋንስ ክፍያ መቋረጥ ይኖርበታል፡፡
- የአገልግሎት ሥራዎች በግዢ መመሪያው መሠረት በውድድር መከናወን ይኖርባቸዋል፡፡

1.2 የዕቃና አቅርቦቶች ክፍያዎች፤

1.2.1.1 ግኝት፣ በዱቤ ሽያጭ ደረሰኝ የተወራረደ ግዢ ክፍያ፤

በፌደራል መንግስት የገንዘብ ክፍያ መመሪያ ቁጥር 4/2003 አንቀጽ 14 ንዑስ አንቀጽ 4 እንደተመለከተው የመንግስት መ/ቤቶች ክፍያ ለሚፈፀምባቸው ወጭዎች ተገቢው የሰነድ ማስረጃ መቅረብ እንዳለበት ይገልጻል፡፡ በዚሁ መሠረት ለግዥ ክፍያዎች ተገቢው ደረሰኝ መቅረቡን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፡-

- ለተለያዩ ዕቃዎችና አገልግሎቶች ግዢ ለተለያዩ አቅራቢዎች (ድርጅቶች) ተከፍሎ በወጪ ለተመዘገበው ብር 20,426,334.68 የቀረበው ማስረጃ የዱቤ ሽያጭ ደረሰኝ መሆኑ ታውቋል፡፡ ዝርዝሩ **በአባሪ ቁጥር 1 ተመልክቷል፡፡**

1.2.1.2 ስጋት፣

በዱቤ ሽያጭ ደረሰኝ የወጪ ሂሳብ እንዲመዘገብ ማድረግ የገንዘብ ክፍያ ደረሰኝ ሲቀርብ ሂሣቡ በድጋሚ በወጪ ሊመዘገብ ይችላል፡፡

1.2.1.3 የማሻሻያ ሀሳብ፣

በዱቤ ሽያጭ ለተመዘገበው የወጪ ሂሳብ የገንዘብ ክፍያ ደረሰኝ እንዲቀርብ እንዲደረግና ለወደፊቱም ተመሳሳይ ሁኔታ እንዳይከሰት ተገቢው ቁጥጥር ሊደረግ ይገባል፡፡

1.2.1.4 የሚመለከተው ኃላፊ ምላሽ፤

የቴክኖሎጂ ኢንስቲትት፣ ፔዳ ግቢ፣ የህክምናና ጤና ሳይንስ ኮሌጅ፣ ግብርናና አካባቢ ሳይንስ ኮሌጅ፣ ቢዝነስና ኢኮኖሚክስ ኮሌጅ እና ግሽ አባይ ግቢ ግብይት ከተፈፀመባቸው ድርጅቶች በተለይ ድሬደዋ የምግብ ኮምፕሌክስ እና የማዕቀፍ ግዥ የዱቤ ሽያጭ ደረሰኝ ተቀብላችኋል ተብሎ የቀረበው የኦዲት ግኝት ትክክልና በአስተማሪነቱ የምንቀበለው ሆኖ ድርጅቶቹ ዕቃውን ገንዘቡ በአካውንታቸው ገቢ ካልሆነ ስለማይሰጡን ችግሩን ለማቃለል በተለይ የምግብ ጉዳይ ጊዜ ስለማይሰጥ ተማሪዎች ለመመገብና የመማር ማስተማሩን ሠላማዊ ለማድረግ ሲባል የተደረገ እንደሆነ በቅንነት እንዲታይልንና ከሁሉም ድርጅቶች ጋር ተነጋግረን በአስተኳይ የገንዘብ ክፍያ ደረሰኝ (Cash sales) ተቀብለን ከሰነዱ ጋር የምናያይዝ መሆኑን እንገልፃለን፡፡

1.2.2.1 ግኝት፣ ያለውድድር በቀጥታ የተፈጸመ ግዢ፤

በፌዴራል የግዥ እና ንብረት አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 649/2001 ምዕራፍ 6 አንቀጽ 52 ተራ ቁጥር አንድ ላይ የመንግስት መ/ቤቶች ከአንድ አቅራቢ ግዥ መፈጸም የሚችሉት በፊደል ‹‹ሀ›› ዕቃው፤ የግንባታ ዘርፍ ሥራው፤ የምክር ወይም ተፈላጊው ሌላ አገልግሎት የሚገኘው ከአንድ ዕጩ ተወዳዳሪ ብቻ በመሆኑ ምክንያት ማወዳደር የማይቻል መሆኑ ሲረጋገጥ ብቻ እንደሆነ ይገልጻል፡፡ ይሁን እንጂ የዩኒቨርሲቲው ሂሣብ ኦዲት ሲደረግ፤

- በማዕከል ግቢ በቀን 21/02/09 በባንክ ወጪ ማስመስከሪያ ቁጥር 79995 በሂሣብ መደብ 6213 ለክረምት ትምህርት አገልግሎት የሚውል ፍራሽና ትራስ ከአማጋ ስፖንጅ ውጤቶች ማምረቻ ድርጅት በብር 6,369,000.00 በቀጥታ ግዥ የተፈጸመ መሆኑ፤
- በኢትዮጵያ ቴክስታይልና ፋሽን ቴክኖሎጂ ኢንስቲትዩት በቀን 20/03/09 በባንክ ወጪ ማስመስከሪያ ቁጥር 1401 በሂሣብ መደብ 6213 በሰላም ግቢ ውስጥ የኔትወርክ ማስፋፍያ ለማድረግ ከላብራዶር አጠቃላይ ንግድ ኃ/የተ/የግ/ማህበር በብር 185,074.28፤

በድምሩ በብር 6,554,074.28 በቀጥታ ግዥ የተፈጸመ መሆኑ በኦዲቱ ወቅት ታውቋል፡፡

1.2.2.2 ስጋት፣

ግዢዎች በደንብና መመሪያ መሠረት ካልተፈጸሙ ዩኒቨርሲቲው በውድድር ማግኘት የሚችለውን ጥቅም እንዲያጣ ያደርጋል፡፡

1.2.2.3 የማሻሻያ ሀሳብ፣

ግዢዎች በደንብና መመሪያ መሠረት እንዲፈጸሙ ማድረግ ይገባል፡፡

1.2.2.4 የሚመለከተው ኃላፊ ምላሽ፤

- **ማዕከል ግቢ፡-** በPV ቁጥር 79995 ለተማሪዎች መኝታ አገልግሎት የሚውል ፍራሽ እና ትራስ በቀጥታ ከአንድ አቅራቢ ግዥ የተፈፀመው ግልፅ ጨረታ ወጥቶ ከአሸናፊው ድርጅት ጋር ውል የተያዘ ቢሆንም በጨረታው ተሳትፎ የነበረ አንደኛዉ ድርጅት በጨረታ ውጤቱ ላይ ቅሬታ በማቅረቡ ቅሬታው ተጣርቶ ውሳኔ እስከሚያገኝ ረጂም ጊዜ በመጠየቁ እና የመደበኛ ተማሪዎች መግቢያ ወቅት በመሆኑ እና ወቅቱ በባሕር ዳር ከተማ ከፍተኛ አለመረጋጋት የታየበት ወቅት በመሆኑ ፍራሽና ትራሱ በወቅቱ ተገዝቶ ባይቀርብ ተማሪዎቹ የሚተኙበት ፍራሽና ትራስ ስለአልነበረ በመስሪያ ቤቱ ላይ የሚያስከትለዉን አደጋ በመገንዘብ

በግዥና ንብረት አስተዳደር አዋጅ አንቀፅ 51 ንዑስ አንቀፅ 1/ ረ ላይ በተገለፀው መሰረት በመስሪያ ቤቱ የበላይ ኃላፊ እንደዚህ አይነት ሁኔታ ሲያጋጥም የቀጥታ ግዥ መፈፀም እንደሚቻል በሚፈቅደው መሰረት በዩኒቨርሲቲው የበላይ ኃላፊ ውሳኔ የተገዛ ነው፡፡ ለማስረጃነት የመንግስት ግዥና ንብረት አስተዳደር የቅሬታ አጣሪ ቦርድ ያስተላለፈውን ውሳኔ እና ጉዳዩን እያጣራ ላለው የፌደራል ፖሊስ ወንጀል ምርመራ ዲቪዥን የተፃፃፍነውን ደብዳቤ 15 ገጽ በአባሪነት ተያይዟል እና ከግኝት እንዲሰረዝልን እንጠይቃለን፡፡(15 ገፅ አባሪ ተራ ቁጥር 8 ይመልከቱ)

- **ኢትዮጵያ ቴክስታይልና ፋሽን ቴክኖሎጂ ኢንስቲትዩት፡-** ኢንስቲትዩቱ ከጅ አይ ዜድ (GIZ) ጋር በፈጠረው መልካም ግንኙነት መሠረት ትላልቅ የኔትወርክ ዕቃዎችን ሙሉ በሙሉ በዕርዳታ ያገኘ ስለሆነ የሰላም ግቢ አዲስ ከመሆኑ ጋር ተያይዞ ለተማሪዎች፣ ለቤተ-መፃሕፍት፣ ለመምህራን እና ለአስተዳደር ሰራተኞች እንዲሁም ለመማር ማስተማሩ ስራ የተሟላ የኢንተርኔት አገልግሎት ለማግኘትና የኔትወርኩን አቅም ለማሳደግ ከዚህም በተጨማሪ በወቅቱ በግንባታ ላይ የነበሩትንና ያልተጠናቀቁትን ግንባታዎች በገመድ አልባ ኢንተርኔት ለማገናኘት ድርጅቱ (GIZ) በራሱ ወጭ ስራውን ያከናወነው ሲሆን ፓስወርዱን ኮንፊገር የማስደረግ እና ሙሉ የኢንስታሌሽን ስራውን ተቋሙ በራሱ ወጭ ማሰራት ስላለበት በተቋሙ ባለሙያዎች እንዲሰራ በተደጋጋሚ የተሞከረ ቢሆንም የኔትወርክ ማስፋፊያውን መስራት ባለመቻላቸው በፌደራል መንግስት የግዥ እና ንብረት አስተዳደር አዋጅ 649/2001 አንቀጽ 51 ንዑስ አንቀጽ 1 ፊደል ተራ "ለ" መሰረት "ተጨማሪ አገልግሎቶችን ከመጀመሪያው አቅራቢ መግዛት ሲፈለግ ወይም ከሌላ አቅራቢ ግዥው ቢፈጸም የሚገዛው አገልግሎት የመንግስት መስሪያ ቤቱ ከሚጠቀምበት አገልግሎት ጋር የማይጣጣም ሆኖ በመገኘቱ ከመጀመሪያው አቅራቢ አገልግሎቱን መግዛት አስፈላጊ መሆኑ በተቋሙ ማኔጅመንት ካውንስል ታምኖበት" ከGIZ የኔትወርክ ባለሙያዎች ጋር የድርድር ኮሚቴ በመምረጥ በከፍተኛ የዋጋ ድርድር የተሰራና ክፍያውም በሚከፈልበት ወቅት የዩኒቨርሲቲውን አይሲቲ ዳይሬክተር ጨምሮ ያካተተ የጥራት ባለሙያ ተቋቁሞ ጥራቱ ተረጋግጦ ህግን መሠረት አድርጎ የተከፈለ ነው፡፡

2. የተሰብሳቢ ሂሳብ፣

2.1 ግኝት፣

የፌደራል መንግስት የሂሳብ አያያዝ መመሪያ ቁጥር 5/2003 አንቀጽ 5 በንዑስ አንቀጽ "ለ" የስራ ማስኬጃ ቅድሚያ ክፍያ በ7 ቀናት ውስጥ መወራረድ እንዳለበትና በንዑስ አንቀጽ "መ" ደግሞ ተሰብሳቢ ሂሳብ በቂ ማስረጃ ሲቀርብለት ብቻ በተሰብሳቢ ሂሳብነት መያዝ ያለበት ሆኖ የተሰብሳቢ ሂሳብ ክምችት እንዳይፈጠር ቁጥጥር ማድረግ እንደሚገባ መመሪያው ቢያመለክትም፤ በሰኔ 30/2009 በተሰብሳቢ ሂሳብ ሪፖርት ከተመለከተው ሂሳብ በድምሩ ብር **8,280,384.39** በጊዜ ገደቡ ያልተወራረደ ሂሳብ የሚገኝ መሆኑ ታውቋል፡፡ ዝርዝር ሁኔታው ቀጥሎ ተመልክቷል፡፡

- በሂሳብ መደብ 4201 (ልዩ ልዩ ቅድመ ክፍያዎች) ለተለያዩ ግለሰቦች ተሰጥቶ በወቅቱ ያልተወራረደ ብር 263,160.18 የሚገኝ መሆኑ፤
- በሂሳብ መደብ 4203 (ለመንግስት ሰራተኞች ቅድሚያ ክፍያ) ከ2001 እስከ 2008 ለሠራተኞች በቅድሚያ ተሰጥቶ ያልተወራረደ ብር 4,666,387.66 የሚገኝ መሆኑ፤
- በሂሳብ መደብ 4210 (በመንግስት መ/ቤቶች ውስጥ ሌሎች ቅድሚያ ክፍያ) በወቅቱ ያልተወራረደ ብር 638,800.51 የሚገኝ መሆኑ፤
- በሂሳብ መደብ 4209 (ለባለበጀት መስሪያ ቤት የሚሰጥ ቅድሚያ ክፍያ) በወቅቱ ያልተወራረደ ብር 142,396.18 የሚገኝ መሆኑ፤
- በሂሳብ መደብ 4211 (የግዥ ቅድሚያ ክፍያ) ከ2001 እስከ 2008 ተሰጥቶ ያልተወራረደ ብር 205,634.40 የሚገኝ መሆኑ፤
- በሂሳብ መደብ 4273 (ከግለሰቦች እና የግል ድርጅቶች ቅድሚያ ክፍያ) በወቅቱ ያልተወራረደ ብር 2,359,982.01 የሚገኝ መሆኑ፤
- በሂሳብ መደብ 4274 (ሌሎች ቅድሚያ ክፍያዎች) ለዩኒቨርሲቲው ሠራተኞች እና ሌሎች በተለያየ ጊዜ ለተለያየ አገልግሎት ተከፍሎ በወቅቱ ያልተወራረደ ብር 4,023.45 የሚገኝ መሆኑ፤ በኦዲቱ ወቅት ታውቋል፡፡

2.2 ስጋት፣

በቅድሚያ ክፍያ ወጪ የተደረገው ሂሳብ በጊዜ ገደቡ ውስጥ አለመወራረድ ለሌላ ስራ ሊውል የሚችለውን የመንግስት ገንዘብ በግለሰቦች፤ በመ/ቤቶችና ድርጅቶች ተይዞ እንዲቆይ የሚያደርግ ከመሆኑም በተጨማሪ ሂሳቡ ወደ ማይወራረድበት ደረጃ ሊደርስ ይችላል፡፡

2.3 የማሻሻያ ሀሳብ፤

ተሰብሳቢ ሂሣቦች በወቅቱ እንዲወራረዱ የዩኒቨርሲቲው ሥራ አመራሩ አፋጣኝ እርምጃ መውሰድ ይኖርበታል፡፡

2.4 የሚመለከተው ኃላፊ ምላሽ፤

- በ4201 እና በ4210 የተመዘገበው ተሰብሳቢ ሂሳብ የመንግስት ሂሳብ ከሲንግል ኢንትሪ ወደ ዳብል ኢንትሪ ሲቀየር እና አድራሻው የማይታወቅ ወይም ከማን ከማን እንደሚሰበሰብ የማይታወቅ ሆኖ ሂሳቡን ለገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር ከአቅም በላይ እንደሆነ አሳውቀን የሰነድ ኮሚቴ ተቋቁሞ ተረጋግጦ ይቅረብ ስለተባለ የሰነድ ኮሚቴው እየመረመረው ያለ ሂሳብ ነው፡፡
- በ4203 ለሰራተኞች በአብዛኛው ለምርምር ስራ ለነዳጅ፤ ለትራንስፖርትና ውሎ አበል ወዘተ ሲሆን በከፍተኛ አመራሩ ውሳኔ መሰረት ሰነድ አቅርበው እየተወራረደና ከደሞዛቸው እየተቆረጠ እየመለሱ ይገኛል፡፡
- በ4209 የተመዘገበው ተሰብሳቢ በብድር ለፕሮጀክት የተሰጠና በ2010 የሚመለስ ነው፡፡
- በ4211 በግዥ ሰራተኛ የተመዘገበ ተሰብሳቢ ሂሳብ አብዛኛው ሰኔ መጨረሻ አቃው ቀርቦ በስራ መደራረብ ምክንያት ሞዴል 19 ሳይቆረጥለት የቀረ ሲሆን በ2010 በአብዛኛው ተወራርዷል፡፡
- በ4273 የተሰጠው ቅድመ ክፍያ ለA.M.B ህንጻ ተቋራጪ 1,147,405.14 እና ለዩሴፍ ተከተል ህንጻ ተቋራጪ 1,131,335.04 የተሰጠ ቅድመ ክፍያ ሲሆን በወቅቱ እንዲመልሱ ተጠይቀው ሊመልሱ ስለአልቻሉ በህግ እንዲጠየቁ ጉዳያቸው ለዩንቨርስቲው ህግ አገልግሎት ቀረቦ ውላቸው በእንግሊዘኛ ስለነበር ወደ አማርኛ ይተርጎም ስለተባለ የተርጉም ስራው ተጠናቆ ክስ ለመመስረት በሂደት ላይ ያለ መሆኑን እንገልፃለን፡፡
- በ4274 የተመዘገበው ተጣርቶ በ2010 በጀት አመት የሚወራረድ መሆኑን እንገልፃለን፡፡

3. በጀት፣

3.1 ግኝት፣

በፌዴራል መንግስት ገንዘብ ክፍያ መመሪያ ቁጥር 4/2003 ክፍል ሁለት አንቀጽ 6/2 መሠረት የበጀት ዝውውር ወይም ተጨማሪ በጀት ካልተፈቀደ በስተቀር ለአንድ የመንግስት መ/ቤት በሂሳብ መደብ ተለይቶ ከተፈቀደው በጀት በላይ ወጪ መፈፀም እንደማይቻል ይገልጻል፡፡ እንዲሁም የተፈቀደው በጀት በአግባቡ ሥራ ላይ መዋል ይኖርበታል፡፡ የዩኒቨርሲቲው የበጀት ሂሣብ ኦዲት ሲደረግ፤

- ለዩኒቨርሲቲው በ2009 በጀት ዓመት የተፈቀደለት በጀት እና በሥራ ላይ የዋለው ሂሣብ ሲነጻጸር በተለያዩ የበጀት ሂሳብ መደቦች ብር 48,864,676.92 ሳይሰራበት ተራፊ ሆኖ ተገኝቷል፡፡
- በ1 የበጀት ሂሳብ መደብ በበጀት ዓመቱ የተፈቀደ በጀት ሳይኖር ብር 120,000.00 ተከፍሎ ተገኝቷል፡፡ ዝርዝሩ **በአባሪ ቁጥር 2** **ተመልክቷል፡፡**

3.2 ስጋት፣

ዩኒቨርሲቲው የታወጀለትን በጀት በወቅቱ አለመጠቀሙ ሊደርስበት ካቀደው ግብ እንዳይደርስ ከማድረጉም በላይ የሀገሪቱን ውስን ሃብት ያለጥቅም እንዲቀመጥ ያደርጋል፡፡ እንዲሁም ከበጀት በላይ መጠቀም ደግሞ ተጠያቂነትን ያስከትላል፡፡

3.3 የማሻሻያ ሀሳብ፣

ዩኒቨርሲቲው የተፈቀደለትን በጀት በመንግስት የፋይናንስ አዋጅ መሰረት በስራ ላይ እንዲያውል እና ከተፈቀደዉ በጀት በላይ ወጪ እንዳይሆን የተቋሙ ሥራ አመራር በበጀት አጠቃቀም ላይ ተገቢውን ክትትልና ቁጥጥር ማድረግ ይኖርበታል፡፡

3.4 የሚመለከተው ኃላፊ ምላሽ፤

- ያልተሰራበት በጀት (ከበጀት በታች)በተመለከተ፤ በ2009 በጀት ዓመት እስከ ሁለተኛው ሩብ ዓመት መረጋጋት ያልነበረና በበጀት ዓመቱ ሊገዙ የታቀዱ ዕቃዎች(አገልግሎቶች) ከግማሽ በጀት ዓመቱ ጀምሮ ጫራታው ወጦ አሸናፊዎች ተለይተው ከድርጅቶች ጋር ውል የተያዘ ቢሆንም አቅራቢ ድርጅቶች በበጀት ዓመቱ አቅርበው ይከፈላል ተብሎ ሲጠበቅ በተለያየ ምክንያት እቃዎችን (አገልግሎቶችን) በበጀት ዓመቱ ሳየቀርቡ ቀርቶ በጀቱን አዛወረን እንኳ እንድንጠቀምበት እስከ ሰኔ 30/2009 እናቀርባለን እያሉ ስንጠብቅ ሳንጠቀምበት በስራ ላይ ያለዋለ ሲሆን ለወደፊቱ ቀድመው እንዲያቀርቡ ይደረጋል ካላቀረቡም አዛውረን የምንጠቀም መሆናችንን እንገልፃለን፡፡
- በጀት በሌለበት የወጪ መደብ የተከፈለው ብር 120,000 በጀት ማዛወር በማንችልበት ወቅት በጣም አስቸኳይ ግዴታ መከፈል የነበረበት ወጪ በመምጣቱ የተከፈለ ነው፡፡ በአጠቃላይ ከላይ የተጠቀሱ ጉዳዮች ድጋሚ እንዳይከሰቱ ትኩረት ሰጥተን እንሰራለን፡፡

4. <u>የንብረት አያያዝና አጠባበቅ፤</u>

4.1.1 <u>ግኝት፤ ህክምናና ጤናሳይንስ ኮሌጅ፤</u>

- ዋጋቸው ሳይገለፅ ከውጭ ሀገር በእርዳታ የመጡ ዕቃዎች በኮሚቴ ዋጋቸው ተተምኖ መመዝገብ ቢገባቸው ዋጋ ሳይወጣላቸው የተመዘገቡ መሆኑ፤
- ዋጋቸው በዶላር ተገልጾ ከውጭ ሀገር በእርዳታ የመጡ ዕቃዎች በሀገሪቱ መገበያያ ገንዘብ (ብር) ሳይቀየር የተመዘገቡ መሆኑ፤
- በአላቂ እና በቋሚ ዕቃዎች ግምጃ ቤት አካባቢ የማገዶ እንጨት ክምችት የሚገኝና ለምግብ ቤት ቅርበት ያለው በመሆኑ አደጋ እንዳያደርስ ተገቢ የማስተካከያ እርምጃ መውሰድ የሚስፈልግ መሆኑ፤
- የአላቂ እና ቋሚ ግምጃ ቤቶች ጠባብ በመሆናቸው ዕቃዎችን በአግባቡ አደራጅቶ ለመጠበቅ የማያስችሉ መሆኑ፤ በኦዲቱ ወቅት ታውቋል፡፡

4.2 <u>ስጋት፤</u>

ዕቃዎች በአግባቡ ካልተመዘገቡና ካልተጠበቁ የመንግስት ንብረት አላግባብ ሊጠፋና ሊባክን ይችላል፡፡

4.3 የ<u>ማሻሻያ ሀሳብ፤</u>

የተጠቀሱት የአሰራር ግድፈቶች እንዲስተካከሉ የዩኒቨርሲቲው ሥራ አመራር ተገቢ የማስተካከያ እርምጃ መውሰድ ይኖርበታል፡፡

<u>**የሚመለከተው ኃላፊ ምላሽ፤**</u>

ለኮሌጁ በእርዳታ የሚመጡ ንብረቶችን ከብዛታቸው አንፃር ዋጋ ተምኖ መላክ ለአንዳንድ በጎ አድራጎት ድርጅቶች ሌላ ጫና በመሆኑ ዋጋ ሳይተምኑ በመላካቸው ኮሌጅ ኮሜቴ በማቋቋም አስጠንቶ ዋጋ መስጠት ስለሚገባ ለወደፊቱ በዚህ አግባብ እንደምናስተካክል እየገለጽን፤ በዶላር የተቀመጠውን ዋጋ ወደ ብር ለመቀየር ግን አሁኑ ወይም ተብሎ በቅንፍ በገባበት ቀን ያለውን የምንዛሬ ዋጋ የምናስቀምጥ መሆኑን እንገልፃለን፡፡

በግምጃ ቤት /በንብረት ክፍል/ አካባቢ ያለውን የማገዶ እንጨት ጉዳይ እና የግምጀ ቤቱን ጥበት በተመለከተ ካለንበት ግቢ የቦታ ጥበት አንፃር ቢታይ እና የቦታ ውስንነት ያለብን መሆኑ ግንዛቤ እንዲወሰድ እንዲሁም አዲስ ግቢ እያስገነባ በመሆኑ በዚህ ግቢ ማስፋፊያ ግንባታ መፈፀም ገንዘብና ጉልበት ማባከን እንደሆነ ታምኖበት ያለውን ክፍል ንብረቶቹ በተገቢው ሁኔታ ሊያስቀምጥ የሚችል ሽልፍ በመስራት የንብረቶችን ደህንነት እያስጠበቅን መሆኑን እንገልፃለን፡፡

6. በተሰጠ የኦዲት አስተያየት መሰረት እርምጃ ያልተወሰደባቸው ግኝቶች በተመለከተ፤

6.1 ግኝት፤

የፌዴራል መንግሥት የፋይናንስ ኃላፊነት መመሪያ ቁጥር 6/2003 አንቀጽ 10ለ እና 10ሐ ሂሣብ ኦዲት ማስደረግን በሚለው ስር «በተሰጠ የኦዲት አስተያየት መሠረት በወቅቱ የእርምት እርምጃዎችን የመውሰድና፣ የተወሰዱ የማስተካከያ እርምጃዎችን ለመስሪያ ቤቱ የበላይ ኃላፊና የኦዲት ሪፖርት ላቀረበው አካል የማሳወቅ ኃላፊነት እንዳለበት» መመሪያው ይገልጻል፡፡ ሆኖም ግን ዩኒቨርሲቲው በ2007 እና 2008 በጀት ዓመት በተሰጠው የኦዲት አስተያየት መሠረት ከዚህ በታች በተገለጹ ግኝቶች ላይ የማስተካከያ እርምጃ ያልወሰደ መሆኑ ታውቋል፡፡

በ2008 በጀት ዓመት የተገኙ ግኝቶች፤

- በዩኒቨርስቲው አማካኝነት ትምህታቸውን ተምረው የውል ግዴታቸውን ካልተወጡ መምህራን መሰብሰብ የነበረበት ብር 3,192,222.34 ያልተሰበሰበ መሆኑ፣
- ለጠቅላላ ሐኪሞችና ስፔሻሊስቶች ከዉስጥ ገቢ የሚከፈለው የማበረታቻና የሙያ አበል ክፍያ እንዲቋረጥ የኦዲት አስተያየት የተሰጠ ቢሆንም ያልተቋረጠ መሆኑ፤

በ2007 በጀት ዓመት የተገኙ ግኝቶች፤

- ዩኒቨርሲቲው በግብርናና አካባቢ ሳይንስ ኮሌጅ ለተማሪዎች ማደሪያ የሚያገለግል ህንጻዎች ግንባታ ከA.M.B ኮንስትራክሽን ሃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር ጋር የሎት 2 ግንባታ በብር 62,114,548.65 በ730 ቀናት እንድጠናቀቅ እና የሎት 4 ግንባታ በብር 40,796,914.49 በ540 ቀናት እንዲጠናቀቅ ውል የያዘ ቢሆንም ግንባታው በመዘግየቱ ምክንያት ሎት ሁለት 49.63% እና ሎት አራት 85.53% ላይ እንደደረሰ የግንባታ ውሉ እንዲቋረጥ የተደረገ ሲሆን እስከ 2007 በጀት አመት ማጠናቀቂያ ድረስ ርክክብ ባለመደረጉ በዩንቨርሲቲው የመማር ማስተማርም ሆነ ሃብት ብክነት ላይ ላደረሰው የጉዳት ካሳ መቀጣቱን (መክፈሉን) የሚገልጽ ማስረጃ ያልቀረበ መሆኑ፤ ታውቋል፡፡

6.2 <u>ስጋት</u> ፣

በተሰጠ የኦዲት አስተያየት መሠረት የማስተካከያ እርምጃ አለመውሰድ በኦዲት ወቅት የታዩ የአሰራር ግድፈቶች እንዳይታረሙ ከማድረጉም ባሻገር ተጠያቂነትን ያስከትላል፡፡

6.3 <u>የማሻሻያ ሃሳብ</u> ፣

በኦዲት ግኝቶች ላይ በተሰጡት የማሻሻያ ሀሳቦች መሰረት አስፈላጊው እርምጃ እንዲወሰድ በድጋሚ እናሳስባለን፡፡

6.4 <u>የሚመለከተው ኃላፊ ምላሽ፤</u>

- የተሰጠው ቅድመ ክፍያ ለA.M.B ህንጻ ተቋራጪ 1,147,405.14 እና ለዩሴፍ ተከተል ህንጻ ተቋራጪ 1,131,335.04 የተሰጠ ቅድመ ክፍያ ሲሆን በወቅቱ እንዲመልሱ ተጠይቀው ሊመልሱ ስለአልቻሉ በህግ እንዲጠየቁ ጉዳያቸው ለዩንቨርስቲው ህግ አገልግሎት ቀረቦ ውላቸው በእንግሊዘኛ ስለነበር ወደ አማርኛ ይተርጎም ስለተባለ የትርጉም ስራው ተጠናቆ ክስ ለመመስረት በሂደት ላይ ያለ መሆኑን እንገልፃለን፡፡

በመጨረሻም ለተደረገልን መልካም የስራ ትብብር እናመሰግናለን!

አባሪ ቁጥር 1. በዱቤ ሽያጭ ደረሰኝ የተወራረደ የግዢ ክፍያ፤

ተ.ቁ	የትምህርት ክፍል/ኮሌጅ	ቀን	የባንክ ወጪ ማስመስከሪያ/ የክፍያ ማዘዣ	የሂሣብ መደብ	ገንዘቡ የተከፈለው ድርጅት	የክፍያው ምክንያት	የገንዘብ መጠን
1	ህክምና ጤና ሳይንስ ኮሌጅ	03/09/09	67232	6244	አልት ከምፒውቴክ	ለኮፒ ማሽን እና ኤልሲዲ ፕሮጅክተር	1,112,004.09
2	ግብርናና አካባቢ ሳይንስ ኮሌጅ	19/08/09	82645	6216	ድሬዳዋ ምግብ ኮምፕሌክስ	ቬራፓስታ	308,739.94
3	››	08/09/09	82689	6313	አልት ከምፒውቴክ	ለኮፒ ማሽን እና ኤልሲዲ ፕሮጅክተር	1,090,845.45
4	››	08/09/09	82691	6313	ዋውፕራይም ሀውስ	ለፋይል ካቢኔት	108,939.50
5	››	15/09/09	85073	6211	አል-አስር ኢንዱስትሪ	ለደንብ ልብስ	245,043.00
6	››	29/07/09	82603	6211	ካንጋሮ ጫማ ፋብሪካ	ለጫማ ግዢ	110,879.41
7	ቢዝነስና ኢኮኖሚክስ ኮሌጅ	09/09/09	72661	6216	ድሬደዋ የምግብ ኮምፕሌክስ	ቬራ ፓስታ	214,999.95
8	ፖሊ ፔዳ ግቢ	29/02/09	00360	6313	ስናፕ ንግድና ኢንዳስትሪ	ለኮምፒዩተር ግዢ	995,145.00
9	››	22/06/09	40784	6218	ከአማ ወረቀት አምራች ኃ/የተ/የግ/ማ.	ለኮምፒተርና የፎቶ ኮፒ ወረቀት ግዢ	306,475.00
10	››	07/02/09	00747	6212	ድሬዳዋ ምግብ ኮምፕሌክስ	ቬራፓስታ	429,999.90
11	››	25/09/09	12904	6213	ፖሊ ፔዳ ኢንተርፕራይዝ	የተማሪዎች መቀመጫ ወንበር	149,999.10
12	››	11/09/09	40841	6213	አልታ ኮምፒዉቴክ ኃ/የተ/የግ/ማህበር	የኤሌክትሮኒክስ እቃዎች	7,678,443.35
13	ቴክኖሎጂ ኢንስቲትዩት	30/06/09	038586	6313	ከአልታ ኮምፒዉቴክ	ለፕሪነረተርና ፕሮጀክተር ግዢ	230,805.00
14	››	30/06/09	038587	6313	Imperial ICT solutions plc	ups 1000 VA ግዢ	251,850.00
15	››	26/05/09	96986	6313	ፖሊ ፔዳ ኢንተርፕራይዝ	ለወንበር ግዢ	449,997.30

16	››	19/11/08	85396	6412	ድሬዳዋ ምግብ ኮምፕሌክስ	ለፓስታ ግዢ	214,999.95
17	››	18/04/09	96828	6218	Repl soap and detergenss.c	ለሣሙና ግዢ	404,528.00
18	››	12/07/09	038641	6212	አልሳምኃ/የተ/የግ/ማ.	ለቢክ እስክሪብቶ ግዢ	247,000.00
19	››	14/07/09	038653	6218	ሶሎዳ የንፅህና እና የወረቀት ዉጤቶች ማምረቻ	ሶፍት ግዢ	167,900.00
20	››	30/05/09	038453	6212	ናኖዳ ስንግድና ኢንድስተሪ	ለፕሪንተር ቀለም ግዚ	110,096.52
21	››	16/02/09	85848	6313	አምሉቴክኩባንያ	ለኮምፒዩተር ግዢ	1,731,599.85
22	››	12/04/09	96787	6313	ዳንቴክኖክራፍት	ለፈርኒቸር ግዢ	1,926,466.02
23	››	13/07/09	038648	6216	ድሬዳዋ ምግብ ኮምፕሌክስ	ለፓስታ ግዢ	214,999.95
24	››	13/08/09	038834	6216	ድሬዳዋ ምግብ ኮምፕሌክስ	ቬራ ፓስታ ግዥ	271,760.00
25	››	29/10/09	004201	6211	እድገት ልብስ ስፌት	የፖሊስተር ቪስከስ	40,954.95
26	››	20/10/09	004128	6212	ፊልከር ትሬዲንግ	ፋይል አቃፊ	158,000.00
27		20/08/09	038859	6211	እድገት ልብስ ስፌት	የፖሊስተር ቪስከስ	608,863.59
28	**ይባብ ግቢ**	30/10/09	242631	6216	ድሬዳዋ ምግብ ኮምፕሌክስ	ለፓስታ ግዢ	644,999.86
						ድምር	**20,426,334.68**

አባሪ ቁጥር 2. የ2009 በጀት ዓመት በጀት ማመዛዘኛ

የወጪ የሂሳብ መደብ	የተስተካከለ በጀት	ስራ ላይ የዋለ ወጪ	ያልተሰራበት በጀት	ከበጀት በላይ ወጪ የተደረገ	ልዩነት %
6113	2,016,384.67	1,548,815.92	467,568.75		23
6133	589,494.59	73,499.92	515,994.67		88
6212	17,812,417.94	16,102,066.01	1,710,351.93		10
6215	20,575,825.18	12,054,008.32	8,521,816.86		41
6218	19,220,153.68	15,069,365.22	4,150,788.46		22
6232	17,097,192.78	13,823,635.46	3,273,557.32		19
6243	4,406,179.00	1,925,194.19	2,480,984.81		56
6251	30,363,163.75	23,821,211.92	6,541,951.83		22
6252	19,433,886.67	12,651,217.41	6,782,669.26		035
6253	6,990,934.10	5,458,615.37	1,532,318.73		22
6255	2,321,250.82	611,735.63	1,709,515.19		74
6257	7,900,453.81	4,407,598.83	3,492,854.98		44
6271	13,580,823.70	5,896,519.57	7,684,304.13		57
6116	55,677,891.61	62,351,343.24		6,673,451.63	12
6213	7,975,884.86	9,286,882.77		1,310,997.91	16
6214	2,677,387.28	3,074,732.15		397,344.87	15
6219	1,081,871.51	1,704,449.60		622,578.09	58
6221	772,478.63	1,027,023.68		254,545.05	33
6233	17,248,066.07	19,591,584.86		2,343,518.79	14
6256	2,511,862.85	8,003,157.59		5,491,294.74	219
6258	11,456,696.00	13,337,679.32		1,880,983.32	16
6313	184,516,106.97	253,592,296.09		69,076,189.12	37
6314	3,514,287.18	4,318,212.08		803,924.90	23
ድምር	**449,740,693.65**	**489,730,845.15**	**48,864,676.92**	**88,854,828.42**	
6416	--	120,000.00	120,000.00		